በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

ጥቅምት 25 ቀን 2007ዓ.ም

## *በስብሰባ ጋጋታ የተማረውን ሕብረተሰ የሸፈተ ልብ ምርኮኛ ማድረግ አይቻልም*

በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ከተቋቋመበት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ያጋጠመውን ዙሪያ ገብ ችግር ፣ በመምህራን ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና በደል ከዚህ አንፃር መምህራን የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅና መብቶቻቸውን ለማስከበር ማድረግ ያለባቸውን እንቅስቃሴና መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃ በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ መግለጫዎችን በማውጣት በመላው ዓለም ላሉ ኢትዮጵያውያን ባጠቃላይና በተለይ ለጉዳዩ ባለቤቶች ለኢትዮያጵያ መምህራን ፣ ለተማሪዎችና ለወላጆች እንዲደርስ አድርጓል።

በዚህ መግለጫ ከላይ በርዕሱ እንደተመለከተው የኢትዮጵያን ሕዝብ በጠመንጃ ኃይል እየገዛ ያለው አምባገነኑ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት በ2007ዓ.ም የምርጫ ዋዜማ ላይ ሆኖ ት/ቤቶችን የፖለቲካ አጀንዳ ማራመጃ ማዕከል በማድረግ የምርጫ ማጭበርበሪያ ስልት ቀድመ ዝግጅት እያመቻቻ እንደሚገኝና የመምህራንና የተማሪዎች ተሳትፎና ምላሽ ምን መልክ እንደነበረው ከደረሱን መረጃዎች ጋር አቅርበናል።

ሥርዓቱ ዳኞችን ፣ ፖሊሶችን የራሱን የድርጅት አባላት፣ የአንደኛና የሁለተኛ ድረጃ ት/ቤቶችና የዩኒቨርስቲ መምህራንን በስብሰባ ጠምዶ ከ2007 ዓ.ም ምርጫ ጋር በተያየዘ ብዙ የትምርት ጊዚያቶችን በመባከንና ከፍተኛ የሐገሪቱን ገንዘብ በማፍሰስ በሰጠው የፖለቲካ ስልጠና በተለይ ከት/ቤቶች በተነሳበት ጠንካራ ጥያቄዎችና ተቃውሞ ዕቅዱ እንዳልሰራ፣ ይልቁንም ፍርሃትና ስጋቱ ጨምሮ በስብሰባ ጋጋታ የተማረውን ሕብረሰብ የሸፈተ ልብ ምርኮኛ ማድረግ እንደማይችል መረዳት ተገዷል። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ወያኔ/ኢህአዴግ የፖለቲካ ስልጠና ወቅት ከሁለተኛ ደረጃና ከዩኒቨርስቲ ተሳታፊ ተማሪዎች ከተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች መካከል የተወሰኑትን ከዚህ በታች እናቀርባለን፡-

- አንድ ፓርቲ ብቻ በተቆጣጠረው ፓርላማ ስለመድለ ፓርቲ መናገር አይቻልም።
- አሁን ባሉት ዩኒቨርስቲዎች ባልተሟሉት የትምህርት መሳሪያዎችና በአንዳንድ ብቃት በሚጎደላቸው መምህራን የሚሰጠው ሥልጠና የተማሪዎችን ክህሎት አያዳብርም።
- ኢትዮጵያ ከክፍፍል ተጠቃሚ ነች ወይ? ምንስ አዲስ ነገር ተገኝቶ ነው ከ1993ዓ.ም ወዲህ አዲሲቱ እየተባለች የምትጠራው?
- ኢትዮጵያ ሊበራሊዝምን ብትከታል የበለጠ መጠቀም አትችልም ነበር ዎይ?



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

.በፖለቲካ ስልጠና ሰነዱ ላይ አፄ ሚኒሊክ ያቀዱትና በዘመነ መንግሥታቸው የተከናወነው ጥሩ ሥራዎች አልተካተቱም፣እንዲያውም ሚኒሊክንና አማራን በትምክህተኝነትና በነፍጠኛነት ፈርጆ ስለሚያጣጥል ሌሎች ብሔሮች በአማራው ላይ ጥላቻ እንዲያድርባቸውና የበቀል እርምጃ እንዲወስዱ መንገድ ከፍቷል።ስልጠናው ተቻችሎ የኖረውን ሕዝብ በማለያየትና በማጋጨት ችግር የሚያባብስ ሆኗል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በእርግጥ ብአዴን አማራን ይወክላልን? ከወከለ በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት ተፈጸመ የተባለውን ማስረጃ ያልተገኘለትን በአጼ በአኖሌ አሩሲ ውስጥ አጼ ሚኒሊክ ጡትና እጅ ሲቆርጡ በሚያሳየው ሐውልት ምረቃ ላይ ብአዴን ለምን ተገኝቶ መረቀ?

- አንቀጽ 39 የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ከተባለ አገሪቱን ከመከፋፈል እንዴት ይታደጋል? እንዲያውም ለመነጣጠል በር ይከፍታል እንጂ።
- በሕገ መንግሥቱ ኃይማኖትና መንግሥት የተለያዩ ናቸው የሚለውን ጥሶ መንግሥት በእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ ለምን ጣልቃ ገባ?
- ገበሬዎች ማዳባሪያ እንዲገዙ ይገዳዳሉ፣ በዚህ ተጠቃሚዎች የወያኔ ኩባኒያዎችና አገሪቱን ማራገፊያ ያደረጉ የውጪ አገር ከበርቴዎች ናቸው ። ይባስ ብሎ ደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ አማራዎች ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸው ተጥሰው እንዲፈናቀሉና የቁም ስቃይ እንዲያዩ ፣ የብዙዎች ሕይወትም እንዲቀጠፍ ተደርጓል።
- ነፃ ፍ/ቤት ፣ ነፃ ፕሬስ አለ ይባላል? ኢኮኖሚውስ እንዴት አደጋ ይባላል? ይህ ስብሰባ ምርጫ ስለደረሰ የተዘጋጀ አይደለም ዎይ? ባጠቃላይ በአገሪቱ መልካም አስተዳደር አለ ብላችሁ ታምናላችሁ? የሚሉና በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ይገኙበታል። ከላይ ለተነሱትና ሌሎች ጥያቄዎች የወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎች የተለመደ የቅጥፈት መልስ ለመስጠት ቢሞክሩም በተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ የተነሳ መስማማትና መግባበት ሳይችሉ ስብሰባው በልዩነት ያለ ውጤት ተጠናቋል። ወያኔ የምሱን ቀምሷል።

ከተማሪዎች ስብሰባ ቀጥሎ በተካሄደው የመምህራን ስብሰባ ከተነሱ ጥያቄዎችና ከቀረቡ አስተያየቶች መካከል ደግሞ፡-

- ኢትዮጵያ ለምን ፓርላሜንታዊ ሆነች? ለምን ፕሬዝዳንታዊ አይሆንም?
- ኢህአዴግ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ/ልማታዊ መንግሥት የመጨረሻ ደረጃ ኒዮ ሊበራሊዝም ነው ብሏል፣ የወደፊት ጉዞው ኒዮሊበራሊዝም ከሆነ ለምን ካሁኑ እያዳበርነው አንሄድም?
- የቀድሞ ነገሥታትን በተለይ ሚኒሊክን ኢህአዴግ በመጥፎ አርአያነት ያስቀምጣል፤ ሚኒሊክ ለኢትዮጵያ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረጉ፣ ሉዓላዊነቷን የጠበቁ፣ አዲሲቷን ኢትዮጵያ የፈጠሩ ፣በዓለም አቀፍ ደረጃ ድንበራችንን ያስጠበቁ ፣ዘመናዊ ሥልጣኔን በአገራችን ያስጀመሩና በዓለማችን ከሚገኙ ምርጥ መሪዎች ተርታ የተሰለፉ ናቸው በማለት አቋማቸውን ገልጸዋል። ኢህአዴግ ያላፉትን መንግሥታት ከመኮነን ውጪ ጥሩ የሰሩትን አንድም ነጥብ ያለማንሳቱን ተችተው ከቀደሙት መንግሥታት ጋር ራሱን ከማናፃፀር ይልቅ ከቴክኖሎጂ አኳያ ከውጪ አገር መንግሥታት ጋር ውድድር ቢገባ የሚሻል መሆኑንንም አመላክተዋል።
- ኢህአዴግ አንቀጽ 39ን የሙጥኝ ብሏል፤ እንዲያውም ውሃ በማይቋጥር ምክንያቱ የሕልውናችን ነው የሚለውም ይሰማል።ሐቁ ግን አንቀጽ 39 አለአስፈላጊና ጎጂ መሆኑን በተጨባጭ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚታዩት የብሄር ግጭቶች ዋቢ ናቸው። በማስረጃነት መምህራን ካነሱት አንዱ ኢህአዴግ በፈጠረው አንቀጽ 39 መስረት የሲዳማ ብሔር ያቀረበው የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጥያቄ ምላሽ አለመሰጠቱ ሕገመንግሥቱን ገዢው የወያኔ ሥርዓት ምን ያህል በሸፋንነት እንደሚጠቀምበት አመለካች ነው ብለዋል።ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንቀጽ 39 መሰረት የቤንሻንጉል መንግሥት የመገንጠል ጥያቄ ቢያቀርብ የአባይ ግድብ ጉዳይ ምን ይሆናል?በሚለው ላይ ጭቅጭቅ ተፈጥሮ ምንም ድምዳሜ ላይ ሳይደርስ በእንጥልጥል ቀርቷል።ከዚህ በመነሳት ኢትዮጵያን የሚገነጣጥል አንቀጽ 39 ከሕገ መንግሥቱ መውጣት አለበት፤ የሕገ መንግሥትም ማሻሻያ ሊደረግ ይገባል በማለት የተቃውሞ ሐሳባቸውን አንጸበርቀዋል።
- የሕዝብ ሀብት የሆነውና በገዢው ወያኔ ፓርቲ ቁጥጥር ስር የሚንቀሳቀሰው ሚዲያና በስሙ የግል ናቸው የሚባሉት የሥርዓቱ ምርኮኛ ሚዲያዎች በዜጎች ላይ የሚፈጸመውን ግፍና በደል በፍጹም አያወጡም፤ የሚነገሩት/የሚሰብኩት መንገድና ሕንፃ ስለመሰራቱና ሥርዓቱን የሚያሞካሹ ጉዳዮችን ብቻ ነው። አገራችንን አስመልክቶ በውጪ ሚዲያዎች የምንሳማቸው እውነታዎች ለምን በአገር ውስጥ ሚዲያዎች አንሰማቸውም ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ተጨባጭ መልስ አልተሰጠም።
- የነፃው ፕሬስ መታገድ ገዢውን የወያኔ ፓርቲ አምባገነን አድርጎታል። የሕግ የበላይነት ለከፍተኛ ባለሥልጣናት ፣ ለፖሊስና ለሠራዊቱ አይሠራም ለምን?

- የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ ሲጨመር የኑሮ ውድነት ተከስቷል፤ በዚህ ሳቢያ የግል ተቀጣሪዎችና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘው አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ተጎጂ ሆኗል። ለዚህ ችግር መፍትሔ መንግሥት ምን አስቧል ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ መልስ የለም።
- ለመምህራን የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ ከሌሎች ጋር ሲወዳደር አነስተኛ ነው። ለምሳሌ በዲግሪ ደረጃ ላሉ የግብርና ባለሙያዎች 69%, ፣ለጤና ባለሙያዎች 67% ፣ ለመምህራን 33% የሆነው እንዴት ነው?
- ት/ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ የፖለቲካ ሥራ እየተሠራ ነው፤ ይህ ሕገ መንግሥቱን ይፃረረል፣ ምክንያቱም ት/ቤቶች ከፖለቲካና ከሃይማኖት ነክ እንቅስቃሴዎች ነፃ ናቸው የሚለው ተጥሶ እንደሚታየው የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የፖለቲካ ሥልጠና ለምን በት/ቤቶች እንዲወስዱ ይደረጋል? መንግሥት ለምን በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ይገባል?
- የትምህርት ጥራት  በየዓመቱ እየቀነሰ መምጣቱና አስጊ ደረጃ መድረሱ በስፋት በመምህራን ማብራሪያ የተሰጠበት ከመሆኑም ባሻገር ለትምህርት ጥራት ፣ ለመምህሩ መብትና ጥቅማጥቅም መከበር መቆም የሚገባው መምህራን ማህበር ለመምህራን የቆመ ሳይሆን የመንግሥት መሳሪያ ሆኖ የመምህራንን መብት ፣ነፃነትና ክብር ያዋረደ ፣በሙስና የተዘፈቀ ፣ በመምህራን መልካም ፈቃድና ይሁንታ ሳይሆን በመንግሥት የተቋቋመ መምህራንን ከቶም ሊወክል የማይችል በመሆኑ በስፋት ተገልጿል።
- የ2002 ምርጫ እንከን የለሽ ነበር ይላል በስልጣን ላይ የሚገኘው ገዥው ፓርቲ ብቻውን ስለተወዳደረ እንከን የለሽ ነበር ያስብላል ወይ? ኢህአዴግ ብስለት ያላቸውና ጠንካራ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን አስጠግቶ ለምን አይሰራም? ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ያደረገ መንግሥት እንዴት ለኢትዮጵያ ያስባል?የበጀት ድጎማ እውን ፍትሃዊ ነውን? ለአናሳ ብሔር እየተባለ የሚከፋፈለው ገንዘብ በትክክል ሥራ ላይ ይውላልን? እኛ ኢትዮዮውያን የሁለት ወንድማቾች ልጆች ነን። የኩሽና የሴም ስለዚህ ለምን አንዱ ብሔር ከሌላው ብሔር ይበልጣል ወይም ያንሳል እያልን እንጨቃጨቃለን? ይህ የብሔር ክፍፍል የተቀየሰው ስልጣን ለማራዘም ብቻ ነው ተብሎ በመምህራን ማብራሪያ የቀረበበት ሲሆን ከልሎች ለምን የተለያዩ ባንዲራ አስፈለጋቸው የሚል ጥያቄም ተነስቶ ከፍተኛ ክርክር አስነስቶ በአጠቃላይ ለተጠየቁ ጥያቄዎችና ለተሰጡ የተቃውሞ ሃሳቦች የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች አሳማኝ መልስ መስጠት አቅቷቸው እርስ በርስ ሳይግባቡ በተቀመጡበት መድረክ ላይ ደንግጠው፣ ፈዘውና አፍጠው የቀሩበትና እርስ በርስ እስከ መደባደብ የደረሱበት ስብሰባ እንደነበረ ለማረጋገጥ ተችሏል። ስብሰባው የተማረውን ሕብረተሰብ ጫፍ የደረሰ የተቃውሞ ሃሳብ በወኔ፣ በእልህና በቁጭት በማቅረብ ለውጥ ፈላጊነቱን እና ለትግል ያለውን ቁርጠኝነት ያስመሰከረበት ነበር ለማለት ይቻላል።

መምህራን እስራት ፣ ወከባ፣ዛቻና ማስፈራራት ሳይበግራቸው  የሙያ ነፃነታቸው ደብዛ በመጥፋቱ እየተቆጩ ከግፈኞችና ከጨከኞች ጋር አንተባበርም ፤ ሆድ አደር ካድሬም አንሆንም በማለት የማስተማር ስራቸውን እየለቀቁ ወደ ሌላ የሥራ ዘርፎችና ወደ ሌሎች አገሮች በመጉረፍ ላይ ይገኛሉ። በ2006 ዓ.ም ብቻ በመላ አገሪቱ 20, 000 ሺ በላይ ልምድ ያላቸው መምህራን ሥራቸውን የለቀቁ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ባስደንጋጭ ሁኔታ ከ8000 በላይ የለቀቁት ከአማራ ክልል ነው። የዚህ ሁሉ መምህራን ፍልስት መንስኤ የትምህርት አስተዳደሩና አመራሩ ሙሉ በሙሉ በፖለቲካ መዳፍ ውስጥ መውደቅና ትምህርት ቤቶች የሥርዓቱ ዋነኛ የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያ መሳሪያ በመሆን በመምህራንና በመማር ማስተማሩ ሥራ የፈጸሙት አገራዊ ወንጀል ነው። ከዚሁ የፖለቲካ ስልጠና ጋር ተያይዞ ስለመምህራን መብት፣ ስለትምህርቱ ሁኔታና ባጠቃላይ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ጠንካራ አቋም ይዘው በመከራከራቸውና በአገርና ሕዝብ ላይ ያንዣንበቡ አደገኛ አዝማሚያዎችን እንዲረግቡ በመንግሥት ስም የተቀመጠውን ቡድን በመጠየቃቸው ብቻ ከአዲስ አበባ ከተማ

1. መላኩ አበበ
2. ደምሰው ይገዙ
3. ይስሐቅ ጉደታ
4. አንዳርጋቸው ምህራቱ
5. ሙለታ ዲንቃ
6. አንተነህ ንጉሴ
7. ዮሐንስ
8. ይማም

የተባሉ ስምንት መምህራን ከስራ  ተባርረዋል። ከስራ የማገጃ ደብዳቤው ለክፍለ ከተማ ቢሮዎች የተጻፈ ሲሆን በይዘቱ " የስልጣና መርህ ግብርን ለማደናቀፍ ስውር አጀንዳ ይዘው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ናቸው " የሚል ሰፍሮበታል።ይህን የወያኔ/ኢህአዴግ እኩይ ተግባር አዲስ ክስተት ባይሆንም በዝምታ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም። የአምበገነኑን ሥርዓት ገጽታ በብዕራቸው የሳሉ ሐያሲያን ከርቸሌ ታጉረዋል፤ የእምነት ነፃነታችን ይጠበቅ ያሉ ሙስሊም ምዕመናን እንዲሁ ዘብጥያ ወርደዋል፤ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ዕጣ ፋንታ ይኸው በእስር ቤት መወርወር

ሆኗል። "ሽብርተኛ " ፣ " ስውር አጀንዳ " ፣ " ጸረ-ሕገመንግሥት " ------የራሱ የወያኔ መንግሥት መገለጫ ጥላሸቶች በንጹሀን ዜጎች ላይ መላከክ ያለመታከት ቀጥሎበታል። መምህራን የሙያ ጓዶቻቸው ላይ የደረሰውን አደጋ ለመከለከል ከጎናቸው መቆም የሚበቅባቸው ሲሆን ባገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚኖሩ ወገኖቻችንና የሰብአዊ መብት ተካራካሪ ድርጅቶች ይህን ግፍና በደል ለማስቀረት አንዲተባበሩ፣ ከስራ ተባረው ለሚሳቃዩትም እንደአስፈላጊነቱ እንዲደርሱላቸው አበክረን እንጠይቃለን።

ከላይ በጥቂቱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ብቃት ያላቸው መምህራን የሙያ ነፃነታቸውን አጥተው ከማስተማር ሙያ እየተገፉ ከተደረገ ድንቁርና እንዲነግስ መጋበዝም ይሆናል። አገር በአላዋቂዎች ( ዕውቀት አልባዎች) እጅ ትወድቅና ታሪክ ይጠፋል፤ ባሕል ይሸረሸራል፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ይደናቀፋል፤ በአጠቃላይ አገርና ሕዝብ ወደ ውድቀት ይመራሉ። ወያኔ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ወቅት ጀምሮ ኢትዮጵያን ለመጉዳት በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ የሚገኘው የአገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ በማበለሸት ረገድ ነው። ይህን አደገኛ ክስተት ለመቀየር የትምህርት ጉዳይ የሚያገባቸው ባለድርሻዎች ማለትም መምህራን ፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች ፣ ሌሎች ባላሙያዎች ባጠቃላይ ሕብረተሰቡ በጋራ ቆመው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።ይህ ሁሉ ምስቅልቅል የሚታየው በመንግሥት ስም የተቀመጠው አካል የሕዝብን ፍላጎት ለማሟላት ቅንነት ፍላጎት የማጣትና በተፃራሪው የመቆም ባህርይ ነው። ሕዝብና የወያኔ መንግሥት ሆድና ጀርባ ሆነዋል።በሂዳቱም የአገሪቱ አንጡራ ሀብት በሙስና ለብክነት ተጋልጧል።የሕዝብ / አገር/ ሉዓላዊነት ተገሷል። ዳር ድንበራችን ተደፍሯል፣ ለም መሬታችን እንደ ጉሊት ድንችና ሽንኩርት በርካሽ የኢትዮጵያ ጠላቶች ለሆኑትና ለሌሎች የውጭ ከበርቴዎች እየተቸበቸቡ የመሬት ዘረፋው አዲስ አበባ ዙሪያ ደርሷል፤ ዳሩ ካልተጠበቀ መሐሉ ዳር ይሆናል ይባል የነበረው በእኛ ላይ መድረሱን መካድ ሞኝነት ነው እንላለን። እርስ  በርስ በማጋጨት ሴራ ተተብትበን ጠብቆ የኖረው ትስስራችን ላልቷል ፤ብሔራዊ ክብራችንም ተደፍሯል።ይህ እንዳለም ሆኖ በሺህ ዘመናት የጎለበተው የአንድነት ቋጠሮ ጠላቶቻችንና ጉዳይ አስፈጻሚዎቻቸው በጠበቁት ደረጃ እንዳንወርድ ጠብቆናል።ይህንን ወያኔን ጠልፎ የሚጥለውን የአንድነት ገመደችንን ማጠናከር ያስፈልጋል።

ለተማሪዎችና ለመምህራን በፖለቲካ ሥልጠናው ወያኔ ርዕዮቱን ሊያጠምቅ ቢያቅድም ውጤቱ የተገላቢጦሽ ሆኖ ሁሉም ነገር ከሽፎበታል። የዚህ የተማረ ማህበረሰብ አቋም ከአምባገነኖችና ከአጫፋሪዎቻቸው በቀር ሚሊዮን ዜጎችን ወካይ ክስተት ነበረ። ሳይማር ላስተማረው ሕዝብ መቆም ፤ አውነትንና ሐቅን ማስቀደም ማለት ይህ ነው። ይህን በተናጠል የሚደረግ እንቅስቃሴ በመወያየት ፣ በመነጋገር፣ በመደማመጥና በመግባባት ወጥ ብሔራዊ አጀንዳ ይዞ መራመድ ግድ የሚልበት ወቅት ላይ ነን። ጉዞው አስቸጋሪ የሆነ፣ ጥረትን፣ ትግልን ፣መስዋዕትነትንና ቆረጥነትን የሚጠይቅ ነው። ከፊታችን የሚደቀነው ጊዜያዊ ችግር ካልተወገደ የስቃይና የመከራው ጊዜ ይራዘማል። የማዘናጊያ ስብሰባ ፣ የማደናገሪያ ፕሮፖጋንዳ፣ በሀሰት የሚፈበረክ ዶኮሜንታሪ ፊልም የሕዝቡን ቀልብ እንዳልሳበ መረዳት ተችሏል ። ከዚህም በመነሳት መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ላይ በመሆን የቡርኪናፋሶ ህዝብ ለ26 ዓመታት በውጭ መንግስታት እየታገዘ በጨንቃቸው ላይ ተንሰራፍቶ የተለያዩ በደሎችንና ደማቸውን  ሲመጥ የነበረውን አምባገነኑን የቤይሴ ኮምፓኦሬን (Baise Compaore) መንግሥት በቅርቡ በአጭር ቀናት ውስጥ ከሥልጣን እንዳስወገደው ሁሉ የወያኔን ዘረኛና ዘራፊ መንግሥት ለማሰወገድ ለሚደረገው ትግል ሁሉ በቅድሚያ በስልት መደራጀት እንዳለብን በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪውን ያስተላልፋል።

መምህራን በትግል መብታቸውን ያስከብራሉ!!!

ለመብት መከበር የጋራ ትግል!!

መደራጀት፣ መደራጀት፣ አሁንም መደራጀት የጊዜው ጥያቄ ነው!!!